# ስለሰብአዊ፡መብቶች፡
# ለማስተማር፡የሚረዱ፡
# አንዳንድ፡ዘዴዎች።

በዩኔስኮ ተዘጋጅቶ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ኮሚሽን ተተረጎመ

አንቀጽ ፡ ፩ ፤

የሰው ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ሲወለድ ፡ ነጻና ፡ በክብርና ፡ በመብትም ፡ እኩልነት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ የተፈጥሮ ፡ የማስተዋልና ፡ ሕሊናው ፡ ስላለው ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ በወንድማማችነት ፡ መንፍስ ፡ መመልከት ፡ የገባዋል ።

አንቀጽ ፡ ፪ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የዘር ፡ የቀለም ፡ የጾታ ፡ የቋንቋ ፡ የሃይማኖት ፡ የፖለቲካ ወይም ፡ የሌላ ፡ ዓይነት ፡ አስተሳሰብ ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የኅብረተሰብ ፡ ታሪክ የሀብት ፡ የትውልድ ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ ደረጃ ፡ ልዩነት ፡ ሳይኖሩ ፡ በዚሁ ፡ ውሳኔ የተዘረዘሩት ፡ መብቶችንና ፡ ነጻነቶች ፡ ሁሉ ፡ እንዲከበሩለት ፡ ይገባል ።

ከዚህም ፡ በተቀረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከሚኖርበት ፡ አገር ፡ ወይም ፡ ግዛት ፡ የፖለቲካ ፡ የአገዛዝ ፡ ወይም ፡ የኢንተርናሽናል ፡ አቋም ፡ የተነሳ ፡ አገሩ ፡ ነጻም ፡ ሆነ ፡ በሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ እራሱን ፡ ችሎ ፡ የማይተዳደር ፡ አገር ፡ ተወላጅ ፡ ቢሆንም ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ገደብ ፡ያለው ፡ አገዛዝ ፡ ሥር ፡ ቢሆንም ልዩነት ፡ አይፈጸምበትም ።

አንቀጽ ፡ ፫ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የመኖር ፡ የለጻነትና ፡ በሰላም ፡ የመንሩ ፡ መጠበቅ ፡ መብት አለው።

አንቀጽ ፡ ፬ ፤

ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በባርነት ፡ አይገዛም ። ባርነትና ፡ የባሪያ ፡ ንግድም በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ክልክል ፡ ነው።

አንቀጽ ፡ ፭ ፤

ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ የጭካኔ ፡ ስይ ፡ እንዳይደርስበት ፡ ወይም ፡ ከሰብዓዊ አፈጻጸም ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ የያዋርድ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ ቅጣት ፡ አይፈጸምብትም ።

አንቀጽ ፡ ፮ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በሰው ፡ ዘርነቱ ፡ የመታወቅ ፡ መብት አለው ።

አንቀጽ ፡ ፯ ፤

ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እኩል ፡ ነው ። ያለአንዳች ፡ ልዩነትም ፡ ሕጉ ደህንነቱን ፡ እንዲጠበቅለት ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ መብት ፡ አለው ። ይህንን ፡ ውሳኔ በመጣስ ፡ ከሚደረግ ፡ ልዩነት ፡ ለማድረግ ፡ ከሚነሳሳ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ሁሉም ፡ የእኩል መብት ፡ አለው ።

አንቀጽ ፡ ፰ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ የተሰጡትን ፡ መሠረታዊ ፡ መብቶች ፡ ከሚጥሱ ፡ ድርጊቶች ፡ ከፍተኛ ፡ በሆኑ ፡ ብሔራዊ ፡ የፍርድ ባለሥልጣኖች ፡ ፍጹም ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ እንዲወገድለት ፡ መብት ፡ አለው ።

አንቀጽ ፡ ፱ ፤

ማንም ፡ ሰው ፡ የለፍርድ ፡ ተይዞ ፡ እንዲታሰር ፡ ወይም ፡ በግዛት ፡ እንዲኖር አይደረግም ።

አንቀጽ ፡ ፲ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በመብቶቹና ፡ በግዴታዎቹ ፡ አፈጻጸም ፡ እንዲሁም ፡ በሚከሰስበት ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ለጻ ፡ በሆነና ፡ በማያዳላ ፡ የፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ በትክክለኛና ፡ በይፋ ፡ ጉዳዩ ፡ እንዲሰማለት ፡ የሙሉ ፡ እኩልነት ፡ መብት ፡ አለው ።

አንቀጽ ፡ ፲፩ ፤

፩/ በወንጀል ፡ ክስ ፡ የተከሰሰ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ለመከላከያው ፡ አስፈላጊዎች የሆኑትን ፡ ሁሉ ፡ አቅርቦ ፡ በሚከራከርበት ፡ የይፋ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ወንጀለኛ ፡ መሆኑ ፡ እስቲረጋገጥበት ፡ ድረስ ፡ ከወንጀል ፡ ነጻ ፡ እንደሆነ ፡ የመቆጠር ፡ መብት ፡ አለው ።

፪/ ማንም ፡ ሰው ፡ በብሔራዊ ፡ ወይም ፡ በኢንተርናሽናል ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ወንጀል ፡ ሁኖ ፡ ባልተደነገገበት ፡ ጊዜ ፡ በፈጸመው ፡ ወይም ፡ ባልፈጸመው ፡ ማንኛውም ፡ ሥራ ፡ ወንጀለኛ ፡ ሁኖ ፡ አይከሰከስም ። ወይም ፡ ወንጀሉ ፡ በተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ከተደነገገው ፡ ቅጣት ፡ ይበልጥ ፡ አይፈረድበትም ።

አንቀጽ ፡ ፲፪ ፤

ማንም ፡ ሰው ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ በቤተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ በቤቱ ፡ ወይም ፡ በሚጻጻፈው ፡ ደብዳቤ ፡ በፍርድ ፡ ያልተለየ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ወይም ፡ ክብሩን ፡ የሚነካና ፡ ስሙን ፡ የሚያጎድፍ ፡ ተቃውሞ ፡ አይፈጸምበትም ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ወይም ፡ የሚጎዳ ፡ ተግባር ፡ ሕግ እንዲከላከልለት ፡ መብት ፡ አለው ።

አንቀጽ ፡ ፲፫ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በየብሔራዊ ፡ ወሰን ፡ ክልሉ ፡ የመዘዋወርና ፡የመኖር ፡ ነጻነት ፡ መብት ፡ አለው።

፪/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከማንኛውም ፡ አገር ፡ ሆነ ፡ ከራሱ ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ የመመለስ ፡ መብት ፡ አለው።

አንቀጽ ፡ ፲፬ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከጭቆና ፡ ሸሽቶ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጥገኝነትን ፡ የመጠየቅና ፡ በደህና ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ አለው።

፪/ ፖለቲካዊ ፡ ካልሆኑ ፡ ወንጀሎች ፡ ወይም ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ዋና ፡ ዓላማዎችን ፡ ከሚቃረኑ ፡ ሥራዎች ፡ የተነሳ ፡ በሚደርሱ ፡ ክሶች ፡ ምክንያት ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ ሊያገለግል ፡ አይችልም።

አንቀጽ ፡ ፲፭ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የዜግነት ፡ መብት ፡ አለው።

፪/ ማንም ፡ ሰው ፡ ያለፍርድ ፡ ዜግነቱ ፡ አይወሰድበትም ፡ ወይም ፡ ዜግነቱን ፡ የመለወጥ ፡ መብት ፡ አይነፈገውም።

አንቀጽ ፡ ፲፮ ፤

፩/ አካለ ፡ መጠን ፡ የደረሱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በዘር ፡ በዜግነት ፡ወይም ፡ በሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ ሳይወሰኑ ፡ ጋብቻን ፡ የመፈጸምና ፡ ቤተሰብን ፡ የመመሥረት ፡ መብት ፡ አላቸው ፤ ጋብቻ ፡ በመፈጸም ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜና ፡ ጋብቻ ፡ በሚፈርስበትም ፡ ጊዜ ፡ እኩል ፡ መብት ፡ አላቸው።

፪/ ጋብቻ ፡ የሚፈጸመው ፡ ጋብቻ ፡ ለመፈጸም ፡ በሚፈልጉ ፡ ሁለቱም፡ወገኖች ፡ በሚያደርጉት ፡ ነጻና ፡ ሙሉ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው።

፫/ ቤተሰብ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ የተፈጥሮና ፡ መሠረታዊ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነ ፡ በኅብረሰቡና ፡ በመንግሥቱም ፡ ደህንነቱ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ይገባል ።

አንቀጽ ፡ ፲፯ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ሁኖ ፡ የኅብረት ፡ ባለቤትነት ፡ መብት ፡ አለው።

፪/ ማንም ፡ ሰው ፡ ያለፍርድ ፡ ንብረቱ ፡ አይወሰድበትም።

አንቀጽ ፡ ፲፰ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሃሳብ ፡ የሕሊናና ፡ የሃይማኖት ፡ ነጻነት ፡ መብት፡አለው ፡ ይህም ፡ መብት ፡ ሃይማኖቱን ፡ ወይም ፡ እምነቱን ፡ የመለወጥ ፡ ነጻነትንና ፡ ብቻውን፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ በይፋ ፡ ወይም ፡ በግል ፡ ሁኖ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ወይም ፡ እምነቱን ፡ የማስተማር ፡ በተግባር ፡ የመግለጽ ፡ የማምለክና ፡ የማክበር ፡ ነጻነትን ፡ ይጨምራል።

አንቀጽ ፡ ፲፱ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የሐሳብና ፡ ሐሳቡን ፡ የመግለጽ ፡ መብት ፡አለው ፡ይህም ፡ መብት ፡ ያለጣልቃ ፡ ገብነት ፡ በሐሳብ ፡ የመጽናትንና ፡ ዜናን ፡ ወይም ፡ ሐሳቦችን ፡ ያላንዳች ፡ የድንበር ፡ ገደብ ፡ የማግኘትን ፡ የመቀበልንና ፡ ወይም ፡ የማካፈልን ፡ ነጻነትም ፡ ይጨምራል።

አንቀጽ ፡ ፳ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሰላም ፡ የመሰብሰብና ፡ ግንኙነት ፡ የማድረግ ፡ ነጻነት መብት ፡ አለው ።

፪/ ማንም ፡ ሰው ፡ የአንድ ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ እንዲሆን ፡ አይገደድም ።

አንቀጽ ፡ ፳፩ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ ነጻ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ በተመረጡ ፡ እንደራሴዎች ፡ አማካዮነት ፡ በአገሩ ፡ መንግሥት ፡ የመካፈል ፡ መብት ፡ አለው ።

፪/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በአገሩ ፡ የህዝብ ፡ አገልግሎት ፡ እኩል ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

፫/ የመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ መሠረቱ ፡ የሕዝቡ ፡ ፈቃድ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ .....ይህም ፡ ፈቃድ ፡ ለሁሉም ፡ እኩል ፡ በሆነ ፡ በምሥጢር ፡ በሚደረግ ፡ የድምፅ ፡ መስጠት ፡ ምርጫ ፡ ወይም ፡ በተመሳሳይ ፡ ሁኔታ ፡ በየጊዜውና ፡ በትክክል ፡ በሚፈጸሙ ፡ ምርጫዎች ፡ እንዲገለጽ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

አንቀጽ ፡ ፳፪ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ አባል ፡ እንደመሆኑ ፡ በኅብረ ፡ ሰብ ፡ ደህንነቱ ፡ እንዲጠበቅ ፡ መብት ፡ አለው ፡ እንዲሁም ፡ በብሔራዊ ፡ ጥረትና ፡ በኢንተርናሽናል ፡ መተባበር ፡ አማካይነትና ፡ በእያንዳንዱ ፡ መንግሥት ፡ ድርጅትም ፡ የሀብት ፡ ምንጮች ፡ መሠረት ፡ ለክብሩና ፡ ለሰብዓዊ ፡ አቅሙ ፡ ነጻ ፡ እድገት ፡ የግድ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑት ፡ የኤኮኖሚ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ የባህል ፡ መብቶች ፡ በተግባር ፡ እንዲገለጹለት ፡ መብት ፡ አለው።

አንቀጽ ፡ ፳፫ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የመሥራት ፡ የሥራ ፡ ነጻ ፡ ምርጫና ፡ ለሥራም ፡ ትክክለኛና ፡ ተስማሚ ፡ የአሠራር ፡ ሁኔታዎችና ፡ ሥራም ፡ እንዳያጣ ፡ መብት ፡ አለው

፪/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ያላንዳች ፡ ልዩነት ፡ ማድረግ ፡ ለአንድ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ ደመወዝ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው።

፫/ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ለእራሱና ፡ ለቤተሰቡ ፡ ለሰብዓዊ ፡ ክብር ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ኑሮን ፡ የሚያስገኝለትና ፡ ካስፈለገም ፡ በሌሎች ፡ የኅብረሰብ ፡ ደህንነት ፡ መጠበቂያ ፡ ዘዴዎች ፡ የተደገፈ ፡ ትክክለኛና ፡ ተስማሚ ፡ ዋጋውን ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ።

፬/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ጥቅሞቹን ፡ ለማስከበር ፡ የሙያ ፡ ማኅበሮችን ፡ ለማቋቋምና ፡ ማኅበርተኛ ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ አለው።

አንቀጽ ፡ ፳፬ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡የዕረፍትና ፡ የመዝናናት ፡ እንዲሁም ፡ በአግባብ ፡ የተወሰኑ ፡ የሥራ ፡ ሰዓቶች፡ እንዲኖሩትና ፡ በየጊዜው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜያትን፡ ከደመወዝ ፡ ጋር ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው።

አንቀጽ ፡ ፳፭ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ለእራሱና ፡ ለቤተሰቡ ፡ ጤንነትና ፡ ደህንነት ፡ ምግብ ፡ ልብስ ፡ ቤትና ፡ ሕክምና ፡ አስፈላጊ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አገልግሎቶችም ፡ ጭምር ፡ የሚበቃ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ። ሥራ ፡ ሳይቀጠር ፡ ቢቀር ፡ ቢታመም ፡ ለመሥራት ፡ ባይችል ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ቢሞት ፡ ቢያረጅ ፡ ወይም ፡ ከቁጥጥሩ ፡ ውጭ ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ መሰናከል ፡ ቢገጥመው ፡ደህንነቱ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ መብት ፡ አለው።

፪/ ወላድነትና ፡ ሕጻንነት ፡ ልዩ ፡ ጥንቃቄና ፡ እርዳታ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አላቸው ፤ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ ያለጋብቻ ፡ የሚወለዱ ፡ ሕጻናትም ፡ የተመሳሳይ ፡ የደህንነታቸው ፡ መጠበቅ ፡ መብት ፡ አላቸው።

አንቀጽ ፡ ፳፮ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የመማር ፡ መብት ፡ አለው ፡ ትምህርት ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በአንደኛ ፡ ደረጃና ፡ በመሠረታዊ ፡ ደረጃዎች ፡ በነጻ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ፡ የአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ መማር ፡ ግዴታ ፡ ነው ፡ የቴክኒክና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሙያ ፡ ትምህርት ፡ በጠቅላላው ፡ የከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደግሞ ፡ በችሎታ ፡ መሠረት ፡ ለሁሉም ፡ እኩል ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።

፪/ ትምህርት ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሁኔታ ፡ ማሻሻያና ፡ ለሰብዓዊ ፡ መብቶችም ፡ መሠረታዊ ፡ ነጻነቶች ፡ ክብር ፡ ማዳበርያ ፡ የሚውል ፡ መሆን ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ የተለያየ ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ ሃይማኖት ፡ ባሏቸው ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ሁሉ ፡ መግባባትን ፡ ተቻችሎ ፡ የመኖርንና ፡ የመተባበርን ፡ መንፈስ ፡ የሚያጠነክርና ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ሰላምን ፡ ለመጠበቅ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ተግባሮች ፡ እንዲስፋፉ ፡ የሚያበረታቱ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

፫/ ወላጆች ፡ ለልጆቻቸው ፡ ለመስጠት ፡ የሚፈልጉትን ፡ ትምህርት ፡ ለመምረጥ ፡ የቅድሚያ ፡ መብት ፡ አላቸው ።

አንቀጽ ፡ ፳፯ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በኀብረ ፡ ሰቡ ፡ የባህል ፡ ኑሮ ፡ በነጻ ፡ መካፈልና ፡ በኪነ ፡ ጥበብ ፡ ለመጠቀም ፡ በሳይንስ ፡ እርምጃና ፡ በጥቅሞቹም ፡ ለመሲቲፍ ፡ መብት ፡ አለው ።

፪/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከደረሰው ፡ ማንኛውም ፡ የሳይንስ ፡ የድርሰትና ፡ የኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡ የሚያገኘው ፡ የሞራሉንና ፡ የሃብት ፡ ጥቅሞች ፡ እንዲከበሩለት ፡ መብት ፡ አለው ።

አንቀጽ ፡ ፳፰ ፤

እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረሀሩት ፡ መብቶችና ፡ ነጻነቶች ፡ በሙሉ ፡ በተግባር ፡ እንዲውሉ ፡ ለሚደረግባቸው ፡ የኅብረሰብና ፡ የኢንተርናሽናል ፡ ሥርዓት ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ አለው ።

አንቀጽ ፡ ፳፱ ፤

፩/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የራሱ ፡ ነጻነትና ፡ ሙሉ ፡ መሻሻል ፡ በሚያገኝበት ፡ ኅብረሰብ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጽማቸው ፡ ግዴታዎች ፡ ይኖሩበታል ።

፪/ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በመብቶቹ ፡ በነጻነቶቹ ፡ በሚጠቀምበት ፡ ጊዜ ፡ የሚታገደው ፡ የሌሎችን ፡ መብቶችና ፡ ነጻነቶች ፡ በሚገባ ፡ ለማስከበር ፡ ብቻ ፡ በተደነገጉ ፡ ሕጎችና ፡ የግብረ ፡ ገብነትን ፡ የመቅላላውን ፡ ሕዝብ ፡ ፀጥታና ፡ ደህንነት ፡ በዴሞክራቲክ ፡ መኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ትክክለኛ ፡ የሆነው ፡ ተፈላጊ ፡ ጉዳይ ፡ ለማርካት ፡ በተዉሰነው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፫/ እነዚህ ፡ መብቶችና ፡ ነፃነቶች ፡ በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ መሠረተ ፡ ዓላማዎች ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መኖጎድ ፡ ሊፈጸሙ ፡ አይገባቸውም ።

አንቀጽ ፡ ፴ ፤

በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ከላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ማናቸውም ፡ መብቶች ፡ ወይም ፡ ነጻነቶች ፡ ለማበላሸት ፡ በታሰበ ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ተግባር ፡ ለማዋል ፡ ወይም ፡ ድርጊትን ፡ ለመፈጸም ፡ ለማንኛውም ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ድርጅት ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ የተባሉ ፡ ህነው ፡ አየተረጎሙም ።